የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሀያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፶፩
አዲስ አበባ መስከረም ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No.51
ADDIS ABABA 28th Sepetember, 2022


**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፭፻፳፩/፪ሺ፲፭


የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣንን አደረጃጀት፡ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ ገጽ ፲፬ሺ፭፻፳፪


**Content**

Regulation No. 521/2022


Definition of Organization, Powers and Duties of Petroleum and Energy Authority Council of Ministers Regulation ……....................Page 14522


## ደንብ ቁጥር ፭፻፳፩/፪ሺ፲፭

## የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣንን አደረጃጀት፡ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌደራል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፶፩ (፪) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣንን አደረጃጀት፡ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፳፩/፪ሺ፲፭"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## REGULATION NO.521 /2022

## COUNCIL OF MINSTERS REGULATION TO PROVIDE FOR DEFINITION OF THE ORGANIZATION, POWER AND DUTIES OF THE PETROLEUM AND ENERGY AUTHORITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers Pursuant to Article 51(2) of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2021.

1. **Short title**

This Regulation may be cited as the "Definition of Organization, Powers and Duties of Petroleum and Energy Authority Council of Ministers Regulation No. 521/2022."


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 84.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001



Scanned with CamScanner

## ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩/ በአዋጅ ቁጥር ፰፻፲/፪ሺ፮ እና ፰፻፴፰/፪ሺ፮ የተሰጡ ትርጉሞች ለዚህም ደንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፪/ "ኢነርጂ" ማለት ከውሀ፣ ከፀሐይ፣ ከነፋስ፣ ከከርሰ ምድር እንፋሎት ወይም ከሌላ ምንጭ የሚገኝ ኃይል ነዉ፤

፫/ "የነዳጅ ውጤት" ማለት ከተፈጥሮ ድፍድፍ ነዳጅ እና ከፔትሮሊየም ጋዝ፣ ባዮ-ፊውል ወይም ሲንተቲክ ነዳጅን ከማጣራት ወይም ከማቀናበር የተገኘ ንፁህ ወይም አግባብ ባለው መንገድ የተደባለቀ የነዳጅ ውጤት ሆኖ ቤንዚንን፤ኬሮሲንን፤ ናፍጣን፣ቀላልና ከባድ ጥቁር ናፍጣንና የአውሮፕላን ነዳጅን ያካትታል፣

፬/ "የግብይት ተሣታፊ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን፤ የሚያስመጣ፣ የሚያጣራ፣ የሚያደባልቅ፣ የሚያከማች፣ የሚያከፋፍል፣የሚቸረችር፣ የሚያጓጉዝ እና መሰል ተግባራትን እንዲያከናውን ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፣

፭/ "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት የነዳጅና የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ለማከናወን የተቋም እና የሙያ ብቃትን በማረጋገጥ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነዉ፤

፮/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

## 2. Definition

In this Regulation unless the context otherwise requires;

1/ Definitions provided under Proclamation No. 810/2013 and Proclamation No.838/2013 are also applicable to this Regulation.

2/ **"Energy"** means power obtained from; water, solar, wind, geothermal or from other sources;

3/ **"Petroleum Products"** means natural crude oil, and natural petroleum gas, biofuel or synthetic petroleum, extracted from crude oil or from blending, or appropriately blended petroleum product like; benzene, Kerosene,gasoil, light and heavy fuel oil and Airplane fuel.

4/ **"Marketing Participant"** means a licensed person who is authorized to perform the functions of importing, refining, blending, storing, distributing, selling transporting of petroleum products and other similar activities;

5/ **"Competency Certificate"** means a certificate issued by the Authority that certify the competency of legal entities and professionals who engage in petroleum and Electrical works;

6/ **"Ministry or the Minister"** means Ministry or the Minister of trade and regional Integration respectively ;

Scanned with CamScanner

፯/ "ባለሥልጣን" ማለት በፌዴራል አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፶፩ (፩) መሠረት የተቋቋመ የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ነው፤

፰/ "ፓናል" ማለት ከባለፈቃዶች ወይም ከደንበኞች ከኤሌክትሪክ አገልግሎት ፣ታሪፍ ፣የአገልግሎት ጥራት ጋር በተገናኘ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በማስማማት ወይም በግልግል ለመዳኘት በባለሥልጣኑ የሚቋቋም ነው፤

፱/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው ሰውነው፤

፲/ ማናቸውም በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ፫. ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## ፬. ዓላማ

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የነዳጅና ኢነርጂ አቅርቦትንና ሥርጭትን ተደራሽነት፣ አስተማማኝነት፣ ፍትሐዊነት፣ ማረጋገጥ፤

፪/ የነዳጅና ኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን እንዲስፋፋ ማስቻል፤

፫/ የነዳጅና ኢነርጂ ዘርፉን ልማትና ተወዳዳሪነት ማስፈን፤

፬/ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊና ግልጽነት ያለው የነዳጅና ኢነርጂ የግብይት ሥርዓት መገንባት፤

7/ **"Authority"** means Petroleum and Energy Authority established Pursuant to Article 51(1) of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2021;

8/ **"Panel"** means a bench established by the Authority to mediate or arbitrate a dispute claimed from licensee or customers pertaining the conditions of supply of electricity, tariff or quality of services,

9/ "Person" means any natural or juridical person;

10/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Head Office

The Authority shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as necessary.

## 4. Objectives

The Authority shall have the following objectives;

1/ Ensure that petroleum and Energy supply and distribution are accessible, reliable and equitable;

2/ Enhance petroleum and energy efficiency and conservation;

3/ Promote development and competitiveness of the petroleum and energy sector;

4/ Build technologically supported modern and transparent petroleum and energy marketing system;

፬/ የነዳጅና ኢነርጂ ተጠቃሚዎችና የአገልግሎት ሰጪዎችን መብትና ግዴታ ማስከበር፡፡

፭. ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በነዳጅና ኢነርጂ ዘርፍ የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ያደርጋል፤ ለሚመለከተዉ አካል ያቀርባል፣ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪/ በነዳጅና ኢነርጂ ዘርፍ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ያከናዉናል፤

፫/ በኢነርጂ ዘርፍ ለሚሰማራ ሰው የሙያና የንግድ ስራ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይተካል፤ ይሰርዛል፤ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣

፬/ በነዳጅ ወይም በኢነርጂ ዘርፍ ለሚሰማራ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይተካል፣ ያግዳል፤ ይሰዛርል፤አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣

፭/ በባለፈቃዱ የሚቀረብለትን ከብሔራዊ ግሪዱ ጋር የተያያዘ ታሪፍ ይገመግማል፤ እንዲፀድቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የውሣኔ ሐሳብ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፤ከብሔራዊ ግሪድ ውጪ የሆኑ ታሪፎች አወሰሰን መመሪያ በማውጣት ያፀድቃል፤ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፤

፮/ የነዳጅ ውጤቶች የዋጋ ግንባታና የግብይት ተሳታፊዎች የትርፍ ህዳግ የአሠራር መመሪያ ያዘጋጃል፣ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደረጋል፤

4/ Enforce the rights and obligations of petroleum and energy consumers and service providers.

5. **Power and Duties**

The Authority shall have the following powers and duties;

1/ Formulate comprehensive legal framework for the petroleum and energy sector, submit to the appropriate organ and Implement upon approval,

2/ Undertake capacity building activities in the petroleum and energy sector,

3/ Issue, regulate, renew, suspend, replace and revoke professional certificate and business license for a person engaged in the energy sector and impose an administrative penalty,

4/ Issue, renew, replace, suspend or revoke competency certificate to a person engaged in petroleum and energy sector and impose administrative penalty,

5/ Review national grid related tariff submitted to it by a licensee and submit its recommendation to Council of Ministers for approval and upon approval, regulate its implementation thereof; issue and regulate the implementation of directives for the determination of off-grid tariffs,

6/ Prepare and submit to the ministry petroleum products wholesale and retail prices and profit margin determination directives and implement upon its approval by the pertinent organ,

፯/ የነዳጅ ውጤቶች የጅምላና የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ እና የግብይት ተሳታፊዎች የትርፍ ህዳግ በማዘጋጀት የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል ፤ በሚመለከተው አካል ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፰/ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የኢነርጂ የብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂና ፕሮግራም በአገር አቀፍ እንዲሁም በዘርፍ ደረጃ ያዘጋጃል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል በየወቅቱ በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት ይገመግማል፤

፱/ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ፣ጥናትና ምርምር፣ልማትና ሠርቶ ማሳያ ተግባራትን ያከናውናል፣ የቁጠባ ባህልን ያስፋፋል፣ ያስተባብራል፤ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግርናበአቅም ግንባታ ዙሪያ ከአገራዊ፤ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሥልጠና ተቋማት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

፲/ የኢነርጂ ኦዲት ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ምልክት ኮድ፤ የብሔራዊ ግሪድ ኮድ፣የደንበኞች አገልግሎት አሠጣጥ ኮድ፣ የኢንስፔክሽን ኮድ የአገልግሎት ጥራት ደረጃ ኮድ፣ የህንፃ ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ኮድ፣ የቴክኒካል ስታንዳርድ ኮድ፤ እና ሌሎች ኮዶችን ያወጣል፤ አፈፃፀማቸውንም ይቆጣጠራል፤

፲፩/ በነዳጅና ኢነርጂ ዘርፍ የሚተገበሩ የቁጥጥር የአሠራር ስታንደርዶችንና ኮዶችን፤ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ይዘረጋል፣እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል፤

፲፪/ የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢ እና የኤሌክትሪክ ኔትወርክ አገልግሎት ስምምነቶችን ያጸድቃል፤

7/ Prepare and submit to the Ministry petroleum products wholesale and retail prices and profit margin of market participants proposal and implement upon approval by pertinent organ,

8/ Prepare long-term, medium-term and short-term energy efficiency and conservation strategy and program at the National and sectorial levels and on the basis of periodic reports to be submitted to it, evaluate the implementation of same,

9/ Promote and coordinate petroleum and energy efficiency and conservation research, demonstration centers, technology transfer. Cooperate and work with National , Regional and international training and capacity building institutions and promote efficient use culture,

10/ Issue energy audit code, energy efficiency standards code, energy efficiency labeling code, national grid code, customers service code, technical inspection code, service quality standard code, building electrical installation code, technical standard code, and other codes and supervise the implementation of same,

11/ Ensure that the regulatory systems and procedures of the petroleum and energy sectors are supported by modern technology, deploy, cause the deployment of technology infrastructure and regulate its implementation,

12/ Approve power purchase and electrical network service agreements,

Scanned with CamScanner

፲፫/ የነዳጅና ኢነርጂ ጥራትና ብቃት ፍተሻ ላብራቶሪዎችን፤ ያቋቁማል፣ የፍተሻ ሥርዓቶችን በማውጣት ይተገብራል፤

፲፬/ ከነዳጅና ኢነርጂ አቅርቦት፤ ሥርጭትና አጠቃቀም ጋር የተዛመዱ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፤ ያሰራጫል፤

፲፭/ የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦትና የሥርጭት ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ለመቆጣጠር የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጅ የተደገፈ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት መከናወኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፮/ አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር የነዳጅ ውጤቶች እና የኢነርጂ የመገልገያ መሳሪያዎች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ እንዲወጣላቸው ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይቆጣጠራል፤

፲፯/ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊኖር የሚገባውን የነዳጅ መጠባበቂያ ክምችት መጠን ይወስናል፤ክምችቱ ስለመኖሩ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤በገበያ ውስጥ የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት በበቂ መጠን መኖሩን ይከታተላል፤በአቅርቦት ላይ ችግር ከተከሰተም የመፍትሔ ሐሳብ ያቀርባል፤ ተፈጻሚነቱንም ይከታተላል፤

፲፰/ በነዳጅና ኢነርጂ ዘርፍ የግብይት መሠረተ ልማትና የሎጀስቲክስ አቅሞች እንዲገነቡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

፲፱/ ከነዳጅ ማከፋፈያ ኩባንያዎች ለራስ ፍጆታ ቀጥተኛ ገዢ የሆኑ ተቋማት የሚያቀርቡትን የነዳጅ ጥያቄ በመገምገም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይፈቅዳል፤

13/ Establish laboratories for petroleum and energy efficiency testing and issue and implement testing procedures,

14/ Collect, organize, analyze and disseminate data related to petroleum and energy supply, distribution, and utilization;

15/ Set procedures supported by modern technology to regulate accessible and fair distribution of petroleum products and follow-up and regulate its implementation,

16/ Cause the setting of mandatory Ethiopian standard for petroleum products in consultation with appropriate body, follow up the implementation same,

17/ In collaboration with pertinent bodies, determine the required volume of petroleum reserve, make sure that the reserve is maintained, follow-up whether there is sufficient supply of petroleum products in the market, propose solution to any problem observed in relation with the supply of petroleum products in the market and follow up the implementation thereof,

18/ In Collaboration with appropriate organs support the development of market and logistics infrastructure in the energy and petroleum sector,

19/ Review the request submitted to it by those institutions to purchase petroleum products directly from oil companies in bulk for self-use and grant permission,

Scanned with CamScanner

፳/ አዳዲስ ማደያዎችና የነዳጅ ዴፖዎች ተገንብተው ወደ ሥራ ለመግባት ዝግጁ መሆናቸውን በማረጋገጥ የነዳጅ ግዢ አገልግሎት እንዲያገኙ ለሚመለከተው ያሣውቃል፤

፳፩/ በነዳጅና ኢነርጂ ዘርፍ በተሰማሩ አካላት ከህጋዊ የሥራ ግንኙነታቸው አንጻር አለመግባባት ሲከሰትና ጉዳያቸውም በባለሥልጣኑ እንዲታይላቸው ሲያመለክቱ በግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አሰራር አዋጁ መሠረት እንዲፈፀም ያስተባብራል፤

፳፪/ እንደ አስፈላጊነቱ ከባለፈቃዶች ወይም ከደንበኞች ከኤሌክትሪክ አገልግሎት ታሪፍ ፣ የአገልግሎት ጥራት ጋር በተገናኘ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በማስማማት ወይም በግልግል ለመዳኘት ባለሥልጣኑ ፓናሎችን ያቋቁማል ፣ሥራቸውንም በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እንዲያከናውኑ ያደርጋል፤

፳፫/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፤

፳፬/ የነዳጅና ኢነርጂ ዘርፍ አገልግሎት አቅራቢዎችንና ተገልጋዮችን መብትና ግዴታ አፈጻጸም ይከታተላል፤ ጉድለት ሲገኝም የማስተካከያ ያደርጋል፤

፳፭/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

## ፮.የባለሥልጣኑ አቋም

ባለሥልጣኑ፡-

፩/ ዋና ዳይሬክተር፤

፪/ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና ፤

፫/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

20/ Ensure the newly constructed petroleum products retail stations and depots meet the requirement to start operation,

21/ When disputes arise among those working in the energy and petroleum sector regarding their legal relationship and if the parties prefer to put a request to the Authority for its resolution, the Authority shall coordinate the resolution of the dispute in accordance with the Arbitration and Conciliation Working Procedure Proclamation;

22/ The Authority as may be necessary shall establish professional panels to mediate or arbitrate a dispute claimed from licensees or clients on electricity service fee, claims pertaining to the quality of the services. Details shall be prescribed by the directive to be issued by the authority;

23/ Collect service fee based on the rate set by the Council of Ministers Regulation,

24/ Follows-up the implementation of the rights and obligations of service providers and consumers in the sector, take appropriate corrective measures wherever gaps are observed,

25/ Perform other activities to achieving its stated objectives.

## 6. Organization of the Authority

The Authority shall have;

1/Director General,

2/ Deputy Director Generals as may be necessary and,

3/ Necessary staff.

Scanned with CamScanner

፯. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ባለሥልጣኑን ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩)አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ)በዚህ ደንብ አንቀፅ ፭ የተጠቀሱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) በፌደራል መንግሥት ሠራተኞች ሕጎች እና በራሱ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ)ባለሥልጣኑን ዓመታዊ ዕቅድ እና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ይተገብራል፤

መ)ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ)ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ)ዓመታዊ ዕቅድና በጀት፣አፈጻጸምና የፋይናንስና የኦዲት ሪፖርቶችን ለሚኒስቴሩና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና ውጤታማነት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ የሥራ ኃላፊዎች ወይም ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

7. **Powers and Duties of the Director General**

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Authority and shall direct and administer the activities of the Authority.

2/ without limiting the generality of sub-Article (1) of this Article, the Authority shall:

a) Exercise the Power and Duties of the Authority referred to in Article 5 of this Regulation,

b) Recruit and administer the Authority's staff in accordance with its own Directives and Federal Civil Servant Laws,

c) Prepare and submit the annual budget and work plan of the Authority and implement same upon approval by the Ministry,

d) Authorizes payments in accordance with approved budget and work plan,

e) Represents the Authority in all its dealing with third parties,

f) Submit the Authority's Annual budget performance and finance, audit report to the Ministry and other concerned parties.

3/ The Director General may delegate part of his Powers and Duties to officials and other employees of the Authority to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Authority.

Scanned with CamScanner

**፰. የምክትል ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር**

፩/ የተመደበበትን የሥራ ዘርፍ ይመራል፣ ያስተዳድራል ፤

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩ በተለይ ካልወከለ በስተቀር በምደባ ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶ ይሰራል፡፡

**፱/ የባለሥልጣኑ የገቢ ምንጮች**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፡-

፩/ባለሥልጣኑ የሚሰበስበው የአገልግሎት ክፍያ፤

፪/ ከመንግሥት የሚመደብ በጀት፤

፫/ የባለሥልጣኑን ተግባር ለማስፈጸም የሚያገኘው ሌላ ገቢ፡፡

**፲. ስለበጀት**

የባለሥልጣኑ ዓመታዊ በጀት በመንግሥት ይፀድቃል፡፡

**፲፩. የሒሣብ መዛግብት**

፩/ ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሣብ መዛግብቶችን ይይዛል፡፡

፪/ የባለሥልጣኑ የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራል፡፡

**8. Powers and Duties of the Deputy Director General**

1/Leads and manages the sector he is assigned to,

2/ carryout other duties specifically assigned to him by the Director General,

3/ In the absence of the Director General and upon delegation shall act in place of the Director General; failing such delegation a Deputy Director General with the longest tenure shall be designated.

**9. Sources of Income**

The Authority shall have the following sources of income:

1/ The fee collected from the service provided by the Authority,

2/ Budget allocated by the Government,

3/ Other income earned to implement the duty of the Authority.

**10. Budget**

The budget of the Authority shall be approved by the Government.

**11. Books of Accounts**

1/ The Authority shall keep complete and accurate book of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of theAuthority shall be annually audited by the Federal Auditor General or an auditor designated by him.

Scanned with CamScanner

**፲፪.ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**12. Effective Date**

This Regulation shall enter into force upon the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 28th Day of Sepetember 2022.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

Scanned with CamScanner

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

Scanned with CamScanner